# የአቶ በረከት በክሱ ጥፋተኛ መባልና የዶክተር ዐብይ ተቃውሞ አልባ መሆን ያሳስበኛል።ክፍል አንድ

**በአዲስ ተስፋ**

እዚህም እዚያም የሚነሱ የአኩራፊዎችን ትንኮሳ በመመልከት  ዛሬም አገራችን እፎይታ አላገኘችም በማለት የሚጨነቁ መኖራቸውን አልዘነጋም። ነገር ግን አሁን ያሉት የጎሳ ትንኮሳዎችና  ግጭቶች የ አኩራፊዎች ብቻም አይደሉም። አገራችንን ለማፍረስ በፖሊሲ፣ በስርዓትና በህገ መንግስት ተደግፎ ሲካሄድ የኖረው የብዙ አስርት አመታት ውጤት ጭምር እንጂ። እንዲያውም በዋናነት የዚህ የዘረኛው አገዛዝ መርዘኛ ጊዜ ጠብቆ እንዲፈነዳ የተቀበረ ቦምብ ነው። በዋናነት የቤንሻንጉል አመለጠኝ ትርክት በዐማራ ቅማንንት ነን የሚሉ ከሰውነት ተራ የወረዱ ኮሚቴ ነን ባዮችን ተዋናይ ያደረገው እንዲሁም የራያን የማንነት ማህተም ለማበላሸት የሚጥረው የህልም ታላቅ አገር መስራቹ የ አዛውንቶች ክበብ የዶክተር አብይ የእግር እሾህ የሆነ ቢመስልም  ዋና አላማው ገና አልፈራረሰም። ሩቅ አዳሪ የሆነውና ታላቅ አገር አፍርሶ ትንሽ አገር ለመስራት የቋመጠው የሌቦች ቡድን እቅዱ ለኢትዮጵያ ህዝብ ይፋ የሆነው በማይገምተውና ባላሰበው ሁኔታ ነው። ምንም እንኳ በርካታ ጋዜጠኞችና የፖለቲካ ሳይንስ ተመራማሪዎች አስቀድመው ለት ሰራ የታሰበችዋን አገር ማንነት  ሊያሳዩን ቢሞክሩም ቆም ብሎ ሊሰማቸውና ሊረዳቸው የፈለገ አልነበረም። የኢትዮጵያ ቴሌቭዥን አጋጣሚ በሚመስል መልኩ ደጋግሞ ትግራይ ከቤንሻንጉልና ጋምቤላ የምትዋሰንበትን ካርታ  ብናይም እውን የዘረኛው ከአማራ የጸዳ አዲስ አገር ነው ብሎ መቀበል ፈጽሞ አልቻልንም ነበር። የወልቃይትና ራያ አማራነት ለማንም ግልጽ ነው። ችግሩ ወልቃይትም ከሱዳንና በሁመራ በኩል ከቤንሻንጉል ጋር የሚገናኝበት መሆኑ ራያም ኢትዮጵያዊነቱን ለአፍታም የማይክደው አፋር  ኩታ ገጠም መሆኑና የህልሟን አገር ካርታ የሚያበላሽ በመሆኑ ነው። እንድሜ ለእነ በረከት ስም ኦንና የቅማንንት ማንነት አስመላሽ የሚባል በገንዘብ የተገዛ ቡድን ስለመኖሩ  በፊት ከብዙ ኢትዮጵያውያን የተሰወረ ነበር። ነገርን ሁሉ በጊዜው እንዲሉ ዛሬ የዚህ ከሃዲ ቡድን ማንነት ተጋልጧል።የቅማንንት ብሎ ኮሚቴም እርቃኑን ቀርቷል። ያ ማለት ግን የቤንሻንጉልና ጋምቤላ  ከትግራይ ጋር መዋሰን አብቅቶለታል ማለት አይደለም።ምክን ያቱ ደግሞ እነ ደብረጽዮን አሁንም ትኩረታቸው ህዳሴው ግድብ ላይ፣ አሁንም ጭንቀታቸው የቅማንንት ማንነት ኮሚቴ ላይ፣ አሁንም የህገመንግስት ይከበር ጩኸታቸው ከሚመሰርቷት ታላቅ አገር ላይ ነው። ራስ ዳሽን ተራራ በትግራይ ክልል ይገኛል በማለት በስርዓተ ትምህርት ቀርጾ ለህጻናት ያስተማረ ቡድን ህልሙን በቀላሉ ይተዋል ብሎ ማሰብ ጅልነት ነው። በዶክተር አብይ አስተዳደር እየወጡ ያሉ ህጎችንም አንዳንዴ በጥርጣሬ መመልከቱ  ለ አገራችን ህዝብ የሚበጅ ይሆናል። ለምሳሌ በዚህ ሰሞን የወጣው የስደተኞች ህግ በፋይናንስ አቅሙ ለተዳከመው  የዐብይ መንግስት ከምእራባውያን ድጎማ ለማግኘት የሚጠቅም ቢሆንም ዜግነትና የስራ ፈቃድ የመሳሰሉ  ከፍተኛ ጎዳዮችን የያዘ በመሆኑ ለህዝብ ውይይት ክፍት መሆን ነበረበት። ከ አጠቃላይ ነዋሪዎቿ የሚበልጥ ስደተኛ ለተሸከመችው ጋምቤላ የወደፊት ዲሞግራፊክ ስትራክቸርና  ባለ ታላቂቷ ትግራዋያን አቃጆች ግባት የማይሆንበት ምክን ያት የለምና።በሃገራችን በወሳኝ ጉዳዮች  ህግ ከማውጣት በፊት ከህዝብ ጋር ውይይት ማድረግ መለመድ ይገባዋል። ስደተኛ የሚበዛባቸው ጋምቤላ ፣ ሶማሊያ አማራና ትግራይ ውስጥ የሚኖሩ ነዋሪዎች ቢያንስ ስለህጉ ማብራሪያ ተሰጥቶ ወይይት መደረግ ነበረበት። ስደተኝነት የአለም አጀንዳ ከሆነ ቆይቷል። የስደተኞችን ሰብ አዊ መብት ለማክበር የተፈራረሙ አገሮች በየጊዜው ደጋፊ ህግ እንደሚያወጡ ቢታዎቅም ህዝባቸውን ግን በሚገባ ያወያያሉ። ከዚህም አልፎ በብዙ አገሮች የምርጫ መከራከሪያ አጀንዳ ይሆናል። እንደዚህ አይነት ታላቅ ርዕሰ ጉዳይን በአጣዳፊ ፓርላማ ህጉን እንዲያጸድቅ ማድረግ ጥርጣሬን ቢያጭር አያስገርምም።ወደ ተነሳሁበት ሃሳብ ስመለስ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ዎይም በ አሁኑ አጠራር ተፎካካሪ ፓርቲዎች በሀገራችን ህልውናቸው እየከሰመ በመምጣቱ ዶክተር አብይ ተቃዋሚ አልባ መሆናቸው ያሳስበኛል። ለመሆኑ ሁሉም ተሳዳጅና ታሳሪ አባላት የነበሯቸው ፓርቲዎች ፋክክራቸው በሃገር ለመኖርና ላለመታሰር ብቻ ነበር ወይ?ኢህ አዴግ የሚባለው ድርጅት ተሸክሞት የመጣውንና በ ሃገራችን ህዝብ

ላይ ጭኖት የኖረውን ርዕዮተ አለም ከስረ መስረቱ የሚቃዎምና ሌላ ተርማጅ ርዕዮተ ዓለም ያለው ጠንካራ ፓርቲ ማቋቋምስ እንዴት አቃተን?ግ ልብ በሆነና ሁሉም ህዝብ የጋራዋል ከሚል ስሜታዊ የዘር ፌዳራሊዝም አያስፈልግም በማለት በሚዲያ ሃሳብን ከመግለጽ የዘለለ በፖሊሲና በጥናት ይህንን ስርዓት ከንቱ የሚያደርግ ህዝቡንም ለለውጥ የሚያነሳሳና ኢህ አዴግ አለኝ ከሚለው ፕሮግራም የበለጠ አስተሳሰብ እኮ ያስፈልገናል። በ አሁኑ ጊዜ ግን የምናየው የምንሰማውና የምናነብበ ተቃዋሚ ናቸው ከሚባሉ የሚዲያ ትንተናዎች ጀምሮ ዐብይንና ስርዓቱን የሚያንቆለጳጵስ ብቻ ነው። ዶክተር ዐብይ እየሄዱበት ያለውን የቋንቋና ዘር አከላለል እንኳ አሜን ብሎ ወደመቀበል የተገፋ ይመስላል። ግልጽነትና ፍት ሃዊነት የጎደላቸው ርምጃዎች ሲዎሰዱ እንኳ በደፈናው ከመደገፍ ውጪ በሙያዊ ትንታኔ የሚቃዎም የለም። ዶክተር ዐብይ አቅም እንዳላቸው ደግመው ደጋግመው ነግረውናል፣ እኛም አምነናቸዋል፤ ነገር ግን ሙሰኞችንና ወንጀለኞችን እየያዙበት ያለው መንገድ ጥርጣሬ ያጭራል። በሃገራችን ተሰምቶ በማይታዎቅ መልኩ ወደ ሃያ የሚጠጉ ባንኮች አንድ ወር ባልሞላ ጊዜ ተዘርፈዋል። የዚህ ዝርፊያ አቀነባባሪ ደግሞ አዲስ አበባ በግልጽና በአጃቢ የሚነሳቀሱ በተሞላቀቀ ሆቴል ተጠልለው የሚኖሩ ከአመታት በፊት ን ጹሃን ዐማሮች ከነነፍሳቸው በገደል እንዲጣሉ ያደረጉ እጃቸው በደም የተነከረ ሰው ናቸው። እኚህ ሰው በሰላም ይንቀሳቀሳሉ ፣ አመጽ ያስተባብራሉ ፣ ባንክ ያዘርፋሉ። በሌላ በኩል ደግሞ የሃገሪቱን ባንዲራ ይዛች ሁ ወጣች ሁ ፣ የ አንድነት መፎክሮችን አስተላለፋች ሁ ፣ ከክልል ወይም ከተቃዋሚ አርማ ይልቅ የሃገር ባንዲራ ይበልጣል አላች ሁ በ አጠቃላይ ኦነግን ተቃዎማች ሁ ተብለው በርካታ የ አዲስ አበባ ወጣቶች ክስ ተመስርቶባቸውና ሳይመሰረትባቸው በ እስር የመማቅቁ እንዳሉ የ አደባባይ ምስጢር ነው። አቶ በረከት ስም ያን ከሰሞኑ ወደ ዐማራ ክልል እስር ቤት ተላልፈው ተሰጠተዋል። በሚከተሉት ሻጥር የተሞላበት ፖለቲካቸው ፣ የኢህ አዴግ መስራችና ቁንጮ ከመሆናቸው ጋር ተያይዞ ህዝቡ በመያዛቸው ደስታውን በመግለጽ ላይ ይገኛል። የአቶ በረከት መያዝ ለብዙዎቻችን የማናውቀው እፎይታ እንዲሰማን አድርጓል።በተለይም የሰው በላው ስርዓት ዲዛይነር ከመሆናቸው ጋር በተያያዝ ራሱ ኢህ አዴግ የተያዘ ያክል ብዙዎቻችን ተደስተናል። አቶ በረከት የሚጠየቁባቸው በርካታ ወንጀሎች እንዳሉ ከማንም የተሰዎረ አይደለም። ብአዴን ከማእከላዊ ኮሚቴ አባልነት ሲያግዳቸው ማመን በማይቻል መንገድ እንዲሁ ህዝብ ተደስቶ ነበር። ነገር ግን እኚህን ሰው የማገዱን ድፍረትና ጉልበት ብአዴን ከየት አመጣው? ይህች ነገር የፖለቲካ ጨዋታ እንዳትሆን የሚሉ አንዳንድ ሰዎች ስጋታቸውን ቢያጋሩም ማንም ሊሰማቸው ፈቃደኛ አልነበረም።ሰውየውም መታገዳቸው ትክክል እንዳልነበረና ለለውጡም ዋነኛ ተዋናይ እንደነበሩ በሚዲያ ብቅ ብለው ድምጻቸ ውን አሰሙ። ነገር ግን የዶክተር ዐብይን መንግስት መቃዎማቸውን ቀጠሉ በሚል ከተለያየ አቅጣጫ ትችቶች ይወዱባቸው ጀመር። በተለይም መቀሌ በተደረገው የምክክር መድረክ ላይ የውጭ ጣልቃገብነት አለ ብለው በመናገራቸው ብዙዎች በቃ ተስፋ መቁረጣቸውን መናገር ጀመረ። ምንም እንኳ እወክለዋለሁ የሚሉትን የዐማራ ህዝብ ትተው በትግራይ ላይ የሚነዛው ዘርን መነሻ ያደረገ ፕሮፓጋንዳ ያሳዘናቸው መሆኑና የዐማራ ክልል ባለስልጣናትም ዘረኛ ቅስቀሳ እያደረጉ መሆናቸውን ሲሞክሩ ብዙዎቻችን ብንቃዎማቸውም ሰውየው ግን ፖለቲካዊ ቁማር የሚችሉ እንደሆኑ መዘንጋት የለብንም። በአንድ በኩል የዶክተር ዐብይ የለውጥ ጉዞ ደጋፊ ነኝ እንዲያውም ዶክተር አብይ አንዳንድ ስራዎችን እያሰራኝ ይገኛል በማለት ተናገሩና ከህወሃት ጄለዎቻቸው ጋር ያላቸውን አጋርነት ለማጠናከር ደግሞ የመቀሌው ምክክር ጥናት ጽሑፍ አቅራቢ ሆነው ብቅ አሉ።

አሁን አቶ በረከት በጥረት ኮርፖሬት አድርሰዋል በተባለው ጥፋት ተጠርጥረው በአማራ ክልል መንግስት በቁጥጥር ስር ላይ ይገኛሉ። በዚህም አብዛኛው ህዝብ በመደሰት ላይ ይገኛል። ወደ አያያቸው ፍት ህ አዊነትና ወደ ተከሰሱበት ርእሰ ጉዳይ ስንመጣ ግን የዶክተር ዐብይን እርምጃ ከመደገፍና ነገሩን ላይ ላዩን ከማየት ውጪ ብዙ ርቀት የሄድን አይመስልም። አንዲት በጣም ቀላል ጥያቄ ላንሳ። የአገሪቱን ፋይናንስ ስርዐት የሚይናጋ ከሃያ በላይ ባንኮችን መዝረፍ ወይስ ጥረት በሚባል አንድ ካምፓኒ ጉዳት ማድረስ የትኛው የበለጠ ወንጀል ይሆን?

በአጭሩ አቶ በረከት የተከሰሱበትን ወንጀል ለመከላከል ለእርሳቸው በተለይም በርካታ ሴራዎችን ሲቋጥሩ ሲፈቱ ለኖሩ ሰው ቀላል ነው። ፍትሃዊ ነው ለማለትም ብዙ ርምጃዎችን መጠበቅ አለብን። አቶ በረከት በትዕዛዝ እስረኛ ያስፈቱ ነበር፣ በትእዛዝ ሰው ያሳስሩ ነበር ፣ የፈለጉትን በአንዲት የስልክ ጥሪ ያከናውኑ ነበር። ይህ ሁሉ ሲሆን ግን ፊርማቸውን ወያም ያዘዙበትን ሰነድ ለማግኘት የማይቻል እንዲሆን አድርገው ያስሩታል። አንዲት

በእኔ በአካል የተፈጸመች ክንውን ላካፍል። ድህረ 97 ምርጫ በአገራችን የነበሩ ሚዲያዎች ፣ በተለይም የህትመት ውጤቶች ከገበያ ወጡ። በጊዜው ከጓደኞቼ ጋር ተመካከርንና አንዲት ጋዜጣ አቋቋምን። የፍይናንስ አቅማችን ብዙም አልነበረም። በዎቅቱ አዲስ ነገር፣ ሰንደቅ፣ ፍት ህ፣ እንቢልታና የእኛ ጉግል ጋዜጣ ብቻ ነበሩ።

በእርግጥ በኋላ ሌሎችም እየጀመሩ የተቋረጡ ለምሳሌ የእነ ዳዊት ከበደ አውራ አምባ፣ መሰናዘሪያና ሌሎችም ጋዜጦች ነበሩ። የእኛ ጉግል ጋዜጣ ከ1998 ዓም መጨረሻ እስከ 2002 ነሃሴ ወር በስራ ላይ ነበረች። የጀመርነው የቅንጅት አመራሮች ከእስር በሚፈቱበት ጊ ስለነበር ከእስረ ሲፈቱ ተከፋፍለው እንደሚዎጡ ለዚህም የአቶ በረከት መንግስት ሰራውን በሚገባ መስራቱን መረጃዎች ነበሩን። በተለይም በዶክተር ብርሃኑና በኢንጅነር ሃይሉ መካከል የተፈጠረውን ልዩነት ዜና ሰርተን የኢትዮጵያን ህዝብ ማሳዘን አልፈለግንም ነበርና የቅንጅትን መሪዎች ኢንተርቪው ለማድረግ በምንሞክርበት ወቅት ከኢንጅነር ሃይሉ ጎን የነበሩ መሪዎች መረጃ ይሰጡን ጀመር ። በተደጋጋሚ ቃለመጠይቅ ያደረግናቸው የቅንጅት መሪዎች የኢንጅነር ሃይሉ ደጋፊዎች በመሆናቸው ከዶክተር ብርሃኑና ወይዘሪት ብርቱካን ጋር የሚሰሩት ደግሞ መረጃ ሊሰጡን አልቻሉም። ስለዚህም የመጀመሪያውን አመት ጋዜጣችን በኢንጅነር ሃይሉ የምትደጎም እየተባለ ትታማ ነበር። ያ ግን ፈጽሞ ሃሰትና ሆን ተብሎ የሚደረግ ሻጥር ስለነበር ከውይዘሪት ብርቱካን መረጃዎችን ለማግኘት ብዙ እንጥር ነበር። በመጨረሻም እንደ እስትራቴጅ ዋና አዘጋጅ በመቀየር ከየትኛውም ኣቅጣጫ የምናገኘውን መረጃ ለማስተላለፍ ሞከርን ። ጋዜጠኛ ውብሸት ታየም የጋዜጣችን ዋና አዘጋጅ ሆነ። በዚህ ጊዜ ደግሞ እነ ወይዘሪት ብርቱካን ከሚመሩት አንድነት ፓርቲ በቂ መረጃዎችን እናገኝ ስለነበረ የወይዘሪት ብርቱካን ጋዜጣ ተባለች። ያም ፈጽሞ ውሸት ነበረ። በነገራችን ላይ በእነዚህ ሁለት አመታት የደረሰብንን ማሸማቀቅ፣ ማስፈራራት፣ ስለላ አንዳናዴም ከፖሊሶችና ከጸረ ሽብር ግብረሃይል የሚሰነዘርብን ማስተንቀቂያና እንግልት ከፍተኛ ነበረ። ጋዜጠኛ ውብሸት ታስሮብን ነበር፣ እኔም ፈደራል ፖሊስ ተጠርቼ ተደብዴያለሁ፣ ጸረ ሽብር ግብረ ሃይልም የተለያዩ እንግልቶችን አድርሶብኛል። ከሁሉ ይልቅ አስቂኝ የነበረው ጋዜጣችን የኢንጅነር ሃይሉ ተብላ ትታማ በነበረበት ጊዜ የወይዘሪት ብርቲካን ደጋፊዎች ነን ከሚሉ ሰዎች ይደርስብን የነበረው ማስፈራሪያና ቦክስ የታከለበት ማስጠንቀቂያ ነው። የመንግስት የስለላ ሰዎች እንደነበሩ ያወቅነው በጣም ቆይተን ነበር።እኔ ልሰደድና ጋዜጣችንም ልት ዘጋ የቻለችበት አጋጣሚ የተፈጠረው ግን በ 2002 ዓም ነበር። ለእኔና ለጋዜጣችን የተመደበው ሰላይ ለ አንድ አመት ስለላውን ካደረገ በኋላ ምሳ ልጋብዘኝ ተስማማን። የማውቀው በስልክ ብቻ ነው። ጋዜጣችን በዎጣች በሰ አታት ውስጥ ይደውልልኛል። ከዚያም ስለ ዜናዎቻችንና ስለ ገበያችን አስተያየት ይሰጠኛል። ደቡብ አፍሪካ ወኪል ሆኖ ሊሸጥልን እንደሚፈልግ ብዙ ጊዜ ያዎራኛል። በመጨረሻም ምሳ ፐላዛ ሆቴል ለመመገብ ተቀጣጠርን። አርብ ጧት ነበር። በዚያ ሰሞን የመንግስታዊው አዲስ ዘመን በብእር ስም የግል ጋዜጦችንና ይዘቶቻቸውን በተከታታይ ይተች ነበር። ፍት ህ ፣ ጉግልና አዲስ ነገር ኢላማዎች ነበሩ። ይህንን ትችት በብእር ስም የሚጽፈው አቶ በረከት ነው ይባል ነበር። እኔን የሚሰልለው ሰው ፐላዛ ምሳ እየበላን ስለትጥቅ ትግል አስፈላጊነት ማውራት ጀመረ። በመጨረሻም አምቦ አካባቢ በአስር ሺዎች የሚቆጠር የተዘጋጀ ቡድን እንዳለውና የእኔ ኔትዎርክ የእርሱን ቡድን እንዲቀላቀል ፋይናንስ ሊያደርጉ የሚችሉ ከውጭ አገር ግንኙነት እንዳለው በማብራራት አወንታየን ጠየቀኝ።እዚህ ላይ ነቃሁ። ነገሩ ወዴት እንደሆነ ገባኝ።እንዲህም አልኩት ። የትጥቅ ትግል ፈጽሞ አያስፈልግም። በምንም መልኩ መፍት ሄ አይሆንም ። ቀዳዳዎችን በመጠቀም ሰላማዊ ትግል ብቻ ነው ማድረግ ያለብን በማለት ጠንከር ብየ አስረዳሁት። ከዚህ ቀን በኋላ ይህ ሰላየ ወደሚቀጥለው እርከን አስተላልፎኝ ከእኔ ተለየ። ከምሳው ግብዣ በኋላ አልደወለልኝም።ከዚህ ትእይንት በመቀጠል የግል ጋዜጦችን የሚተቸው የህትመት ዳሰሳ የተባለው ፕሮግራም በቴለቪዥን ተላለፈ። አዲስ ነገርን፣ ፍት ህንና ጉግልን ማከል አድርጎ የተላለፈው ይህ ፕሮግራም በዋናነት ጋዜጦችን የከስ ሳል። በዚህ ጊዜ በጣም የገረመኝና የእኛ ጋዜጣ ከተከሰሰችበት ርዕሶች አንዱ ራሱ የ አቶ በረከት ቢሮ ኮሙኒኬሽን ጽህፈት ቤት ደውሎ የሰጠን ዜና ይገኝበታል። በጣም ከመናደዴ የተነሳ አቶ በረከት ቢሮ ደወልኩና ሚኒስተሩን ማናገር እፈልጋለሁ የጉግል ጋዜጣ ዋና ስራ አስኪያጅ ነኝ በማለት ቀጥሮ ያዝኩ። በቀጠሮ አችን መሰረትም ዋና አዘጋጃችንን አቶ ኤርሚያስን ይዤ ሄድኩና ቅሬታየን አቀረብክ። ረዥም ሰዓት የፈጀ ውይይት ካደረግን በኋላ ምንም ሊደርስብን እንደማይችልና ስራችንን በሃላፊነት መስራት እንደሚገባን አሳስበውን ወደ ቢሮአችን ተመለስን። ቤቴ ስገባ ልዮ ደብዳቤ ከአቶ

በረከት ቢሮ አገኘሁ። እሁድ በተዘጋጀው የሚዲያዎች የቀጥታ ስርጭት ውይይት በአክብሮት ስለተጋበዙ ማንሳት የሚፈልጓቸውን ነጥቦች ይዘው በውይይቱ እንዲገኙ ተጋብዘዋል የሚል ነበር። ከዚህ ቀጥሎ በምጠቅሳቸው ሁኔታዎች በኮሙኒኬሽን ጽህፈት ቤት

የቅርብ ክትትል እንድንሰራ ከተደረገበት አንድ አመት ገደማ ከሚሞላ ጊዜ ውስጥ የአቶ በረከት ፊርማ ያለበት ትእዛዝ ይህች ወደ ሚድያዎች ውይይት የተጋበዝኩባት ደብዳቤ ብቻ ነች። ሌሎች የሚዘገንኑ ትእዛዞች የሚያደርጉት በቀጥታ ፈጽሞ አይደለም። አንዳንዶችን የሚያስነግሩት ወይም ትእዛዝ የሚያስተላልፉት በሚኒስቴር ዴኤታው ሽመልስ ከማል አማካኝነት ወይም በስልክ ብቻ ነበር።ስለ አቶ በረከት ወንጀል ብዙ ማለት ቢያስፈልግም አሁን ከተከሰሱበትና ሊያስፈርድባቸው ይችላል ከሚባሉ ጥፋቶቻቸው አንጻር ግን የፖለቲካ ሻጥር እንዳይኖር ከምሰጋባቸው ጉዳዮች አንዱን በእኔና በጋዜጣችን ላይ ስለተደረገው አንዲት ማስረጃ ብቻ ላቅርብ። በ2002ዓም በተደረገው ምርጫ የተከናወነ ነው። ጋዜጣችን የኢህ ዐዴግ ነች ተብሎ የተወራበት ወቅት ነበር። ለዚህ ሌላ ጊዜ እኛገራለሁ። እኛ በማንም አልተደጎምንም ይልቁንም የራሳችንን ስምና ገንዘብ ከስረንበታል። በጥሬ ብር ብቻ የራሴን የግሌን ከ ፯ መቶ ሺህ ብር በላይ ከስሬበታለሁ። በተጨማሪም የጋዜጣዋን ህልውና በማየት ብቻ አትራፊ ስለምትመስላቸው ጓደኞቼ ትርፍ የምንከፋፈልበትን ጊዜ ይናፍቁ ነበር። ከሳምንት ሳምንት ለጋዜጠኞቻችን የምንከፍለው ደሞዝ ከየት ይመጣል በሚል ጭንቅ ውስጥ ነበር የማልፈው። ከብዙ ሰዎች ገንዘብ ተበድሬ ከፍየ አውቃለሁ። በመጨረሻም ግንቦት 13, 2002 ዓም ምርጫው ሊደረግ ሁለት ቀን ቀድሞ በ አመቱ ውስጥ ምርጫን በተመለከተ ያደረግናቸውን ቃለመጠይቆች የሚያስታውስ ዋና ዋና ዘናዎችን በክለሳ መልክ ይዘን ወጣን። እጅግ በጣም ጥሩ ዝግጅት ነበር። ከዚህም የተነሳ ከወትሮው በተለየ ጧት ተሽጦ አለቀ። የዚህን ጋዜጣ ይዘት የገመገመው የ አቶ በረከት ቢሮ እኛ ለምርጫው ቀን ማለትም ከ አንድ ቀን በኋላ በሚደረገው ምርጫ ተቃዋሚዎች ወጤቱን መቀበል እንዳለባቸው የሚያሳሰብና የሀይማኖት አባቶችንና የምርጫ ቦርድን ማሳሰቢያ በመጨመር ለህትመት መዘጋጀት እንዳለብን ይወስናል። ውሳኔው የግድ ነበር። ይህንን ውሳኔ ደግሞ አስፈጽሚ ሽመልስ ከማል ነው። አርብ ግንቦት ፩፩ ቀን ከቀኑ ፯ ስዓት ላይ ሽመልሽ ደወለልኝ። በ አስቸኳይ ወደ ቢሮ አቸው እንድሄድም ኮፍጠን ብሎ አዘዘኝ። ሄድኩ ። ለሁለት ሰዓታት ያክል ተከራከርን ። ዓለቃየ አዝዟል ፣ ጋዘጣቹ ሁን ነገ ቅዳሜ ስሩት። እሁድ በ አዲስ ዘመን ኔት ወርክ በነጻ ይታደላል የሚል ቀጭን ትእዛዝ ተሰጠኝ። አዛዡ በረከት አስፈጽሚው ደግሞ ሽመልስ።በመጨረሻም ነገ ቅዳሜ ነው ጋዜጠኞችም ወደ የቤታቸው ሄደዋል፣ ሳምንት በምናደርገው መዘጋጀት የምናሳትመውን ጋዜጣ በ አንዲት ቀን ዝግጅት እንዴት እንችላለን በማለት ሽመልስን ጠየቅ ሁት።ያሳዘነኝና ያስፈራኝ ተስፋም እንድቆርጥ ያደረገኝ ግን ዋና ዋና ከሚባሉት ጋዜጠኞች ህ ጋር ተነጋግረን ተስማምተናል ፤ አሁን የሚጠበቅብህ አስቸኳይ ስብሰባ ጠርተህ ማወያየት ነው። በቃ ጨርሻለሁ። የህትመት ዋጋውን እኛ እንከፍላለን ፣ ለጋዘጣቹ ሁ እንደ ማካካሻ ሶስት መቶ ሺ ህ ብር እንከፍላለን በማለት ከበረከት የወረደውን ትእዛዝ አሸክሞኝ ተለያየን። ወደ ቢሮ ስመለስ እጀግ አዝኘና ተስፋ ቆርጬ ነበር። በውስጤ በ አንድ ነገር ተጽናናሁ። ያ ሶስት መቶ ሺ ህ ብር ቢያንስ ሌት ተቀን ሲደክሙ ለነበሩ ጋዘጠኞች ዳጎስ ያለ ማነቃቂያ እንድከፍላቸው ይረዳኛል በማለት ራሴን በራሴ ላጽናና ሞከርኩ። ለዋና አዘጋጃችን ፤ ለ አማካሪያችን፣ለኤዲትንግ ማናጀሩና ለሁሉም ጋዜጠኞች ስልክ በመደዎል ለስብሰባ አርብ ምሽት ላይ ጠራኋቸው። በጣም የማከብራቸው የስራ ባልደረቦቼ አንድም ሳይቀሩ አስቼኳይ ጥሪየን ተቀብለው ቢሮ ተሰበሰብን።አስቂኙ ነገር ስለሁኔታው አጀንዳ ይዘን ስንነጋገር ዋና ዋና ጋዜጠኞች ህን አነጋግረናቸዋል ፈቃደኛም ናቸው ብሎ ሽመልስ ከነገረኝ ሰወች መካከል የመጀመሪያ የሃሳቡ ተቃዋሚ ሆነው መከራከራቸው ነው። ትልቁ መንግስታችን የሚሰራው ድራማ አይነት መሆኑ ነው። አንዳንድ በቅንነት ስማችንን ገደል ይከታል ከፕሮፌሽናችን ስነምግባር ውጪ ነው ብለው የተከራከሩ ንጽሃንም ነበሩ። በዋናነት ተስማምተዋል የተባሉት ግን እስከ መጨረሻው ተከራከሩኝ። ነገ አንመጣም አንስማማም ብለውም ስብሰባችንን ያለውጤት እንዲበተን ለማድረግ ጫፍ ደርሰው ነበር። እኔም በልቤ ደስ እያለኝ በቃ ጋዜጠኞች አልተስማሙም አንችልም ብየ ለሽመልስ ልደውል ስ ዘጋጅ ድንገት ተስማማን። ጋዜጣው ቅዳሜ ተሰራ ታተመ ወደ 600 ሺ ብር የሚቆጠር ክፍያውንም ለብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ኮሙኒኬሽን ቢሮ ከፈለ። እሁድ ጧት ጉግል ጋዜጣ በነጻ ተሰራጨች። ለ አራት አመታት ደም እየተፋን ያገኘነውን ከሚሊዮን ብር በላይ የሆነው ስማችን ተበላሸ፣ ቃል

የተገባልንን የ300 መቶ ሺህ ብርም አፍንጫችሁን ላሱ ተባልን። አምስት ሳንቲም ሳይከፈለን ሁሉን ማጣት ብቻ ሳይሆን የእኔ ህይዎትም አደጋ ውስጥ ወደቀ። ከአገሬ መወጣት እንኳን በውኔ በህልሜም አስቤው አላውቅም። ይህ ኪሳራና ወንጀል ከተፈጸመብን በኋላ ለምን ከአገር እንድዎጣ እንደሆነ፣ ለምን ሊዎነጅሉኝና ድርጅቴን በአስቼኳይ ጥየ እንድዎጣ እንደተደረገ ፤እለት በእለት የደህንነት ክትትል ለምን እንደተደረገብኝ፣ በአውሮፕላን ወደ ናይሮቢ በምበርበት ቀን እዚያው አየር መንገድ ለሰዓታት ያህል ለምን በቁጥጥር ስር እንደሆንኩ እስካሁን ያልተፈታ እንቆቅልሽ ነው። የዚህ ሁሉ ምስቅልቅል ባለቤት አቶ በረከት ስምዖን ነው፣ ግን ይከሰስ ቢባል በየትኛው አንቀጽና የህግ አግባብ ይከሰሳል? ለዚህ ነው አሁን የተከሰሰበት ክስ በቀላሉ ሊረታበት የሚችል እንደማይሆን የምጠራጠረው።

................የቀጥላል!